## የወንጀልና ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ጠምራ ፣ ክስ ፤

በፊሊፕ ፣ ግሬቨን ፤ ፍርድ ፣ ሚኒስቴር ፣

የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ የካሳ ፣ ክስ ፣ ማለት ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ በሌላው ፣ ሰው ፣ ላይ ፣ ለአ ደረሰው ፣ ጉዳት ፣ የገንዘብም ፣ ሆነ ፤ ሌላ ፣ ጥፋት ፣ የሚከስበት ፣ ማለት ፣ ነው ። (አንቀ ጽ ፣ ፪ሺ፳፰ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ) ። ይህም ፣ ጉዳት ፣ ወንጀል ፣ ወይም ፣ ወንጀል ፣ ላይሆን ፣ ይችላል ። ነገር ፣ ግን ፣ የወንጀል ፣ ጥፋት ፣ ከሆነ ፣ የወንጀልና ፣ የፍትሐ ፣ ብሔ ርን ፣ ጥፋቶች ፣ በአንድ ፣ ላይ ፣ ሊያስከትል ፣ ይችላል ። በአንቀጽ ፣ ፪ሺ፴፭ ፣ እንደተመ ለከተው ፣ መሠረታዊ ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ጥፋ ትን ፣ አጥፍቶ ፣ የሚያልፍበት ፣ አንድን ፣ ግልጽ ፣ የሆነ ፣ ደንብ ፣ በመጣስ ፣ ጉዳት ፣ ያደ ረሰ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ነው ።

ሁለቱም ፣ ዓይነት ፣ ጥፋቶች ፣ በጠባያቸው ፣ ስለሚለያዩ ፣ ከዚህ ፣ የሚነሱት ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ጉዳዮች ፣ በልዩ ፣ ልዩ ፣ ፍርድ ፣ ቤቶች ፣ ይታያሉ ። የወንጀልና ፣ የፍትሐ ፣ ብሔ ር ፣ ዓላማቸው ፣ የተለየ ፣ ሲሆን ፤ ምክንያታቸውና ፣ አስተያየታቸው ፣ የተለየ ፣ ነው ፤ የወንጀሉ ፣ ቅጣትና ፣ የፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ካሳም ፣ የተለዩ ፣ ናቸው ። ነገር ፣ ግን ፣ ሁለቱም ፣ ጥፋቶች ፣ አንድ ፣ በሆነ ፣ ሕገ ፣ ወጥ ፣ ተግባር ፣ ስለሚነሱ ፤ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ የወንጀሉ ንና ፣ የፍትሐ ፣ ብሔሩን ፣ ክስ ፣ በአንድ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ማየት ፣ ለሥራ ፣ ማቀላጠፍ ፣ ይጠቅማል ። የወንጀሉን ፣ ክስ ፣ የሚመለከተው ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ስለ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ካሳም ፣ ሊወስን ፣ ይችላል ። ነገር ፣ ግን ፣ ስለመተዳደሪያ ፣ የሚወስነው ፣ የፍትሐ ፣ ብሔ ር ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ስለወንጀል ፣ ቅጣት ፣ ሊወስን ፣ አይችልም ። ምንም ፣ እንኳ ፣ በወን ጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፯፻፹፭ ፣ ወንጀል ፣ መሥራቱን ፣ እንኳ ፣ ቢያውቅ ፤ ይህ ፣ ወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ በአንቀጽ ፣ ፩፻ና ፣ በወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ሥነ ፣ ሥር ዓት ፣ በአንቀጽ ፣ ፩፻፶፬—፩፻፶፱ ፣ በጉልህ ፣ የተመለከተው ፣ የወንጀልና ፣ የፍትሐ ፣ ብሔ ር ፣ የአንድነት ፣ ክስ ፣ ለኢትዮጵያ ፣ ሕግ ፣ አዲስ ፣ ነገር ፣ አይደለም ። በ፩ሺ፱፻፵፱ ፣ የወን ጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ እንደተመለከተው ፣ የወንጀልን ፣ ክስ ፣ የሚመለከተው ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ የተበደለው ፣ ሰው ፣ ካሣ ፣ እንዲያገኝ ፣ ለማዘዝ ፣ ይችላል ፤ (ለምሳሌ ፣/ አንቀጾች ፣ ፪፻፷፫—፪፻፶፮—፪፻፶፱) ። አዲስ ፣ ሆኖ ፣ የተሠራው ፣ ግን ፣ ሁለቱም ፣ የወንጀልና ፣ የፍት ሐ ፣ ብሔር ፣ ነገሮች ፣ በጣምራ ፣ የሚሠራበት ፣ ጠቅላላው ፣ መሠረት ፣ ነው ። በተጨማ ሪም ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ የጥፋት ፣ ኃላፊነት ፣ በወንጀል ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ የሚሰማበት ፣ ሁኔታና ፣ ሁለቱ ፣ የሚገናኙበት ፣ ሕጋዊ ፣ ሥሪት ፣ ከቀድሞው ፣ ይልቅ ፣ ከፍ ፣ ባለ ፣ ጥን ቃቄ ፣ ተሠርቷል ።

### ፩ ፤ ግዴታዎች ፣

የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ አንቀጽ ፣ ፩፻ ፣ አንድ ፣ ጥፋት ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ ጉዳት ፤ (፩) ከደረ ሰ ፣ የተጐዳው ፣ ሰው ፣ ወይም ፣ ሰዎች ፣ አጥፊው ፣ እንዲከስ ፣ ወይም ፣ እንዲተካ (፪)

---

፩፤ ከፍ ፣ ያለ ፣ ጉዳት ፣ የሚለው ፣ ቢቀር ፣ መልካም ነበር ፤ ምክንያቱም ፣ ጉዳቱ ፣ ትንሽ ፣ ከሆነ ፣ የጣምራ ፣ ካሳ ፣ አይፈቀድም ፣ ማለት ፣ ይመስላል ።

፪፤ የገንዘብ ፣ መተካት ፣ ትእዛዝ ፣ በወንጀለኛ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ለወንጀልና ፣ ለፍትሐ ፣ ብሔርም ፣ በአንድ ፣ ላይ ፣ እንዲታይ ፣ ባይጠቅም ፣ በራሱ ፣ ሊያዝ ፣ ይችላል ፣ (አንቀጽ ፣ ፺፱/፪)ና ፣ ፩፻፶፬ ፣ (፪) ፣ የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ።

ሲል ፡ ተደንግጓል ። ክሱንም ፡ ለማቅረብ ፡ የተጐዱት ፡ ወይም ፡ ካሳ ፡ የሚጠይቁት ፡ ሰዎች ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ የወንጀሉን ፡ ክሶች ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ። የወንጀልና ፡ የፍትሐ ብሔርም ፡ ጣምራ ፡ ክስም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በአንቀጾች ፡ ፩፻፶፬—፩፻፶፱ ፡ በተመለከተው ፡ መንገድ ፡ ወይም ፡ አኳኋን ፡ ይፈጸማሉ ።

፩፤ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፶፬ ፡ (፫)/(፫) ፡ መሠረት ፡ ተጐጂው ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፤ ሕዝብ ፡ በሙሉ ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እራሱ ፡ በማነሳሳት ፡ የጣምራ ፡ ክስ ፡ ይቅረብ ፡ ለማለት ፡ አይችልም ። ነገሩ ፡ በመዠመሪያ ፡ ሲሰማ ፤ ተጐዳሁ ፡ ያለው ፡ ወገን ፡ በማመልከቻ ፡ (፩፻፶፬/፩) ፡ (፬) ፡ በፊት ፡ የጣምራ ፡ ክስ ፡ ይታይልኝ ፡ ብሎ ፡ ማመልከት ፡ አለበት ፡ (፭) ።

አንዳንድ ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ ካልተፈጸሙ ፡ በስተቀር ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ብሔር ፡ ጉዳዮች ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ በጣምራ ፡ መታየት ፡ የለባቸውም ፡ ከተባለ ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ መፈጸም ፡ አለመፈጸማቸውን ፡ ለይቶ ፡ ለመወሰን ፡ ማመልከቻው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ይረዳዋል ። በዚህም ፡ አኳኋን ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፶፬ ፡ ማመልከቻው ፡ (ሀ) ፡ የተፈለገውን ፡ የካሳ ፡ ዓይነት ፡ ለምሳሌ ፡ ምትክ ፡ ወይም ፡ ካሳ ፡ ወይም ፡ ሁለቱን ፡ (ለ) ፡ የተፈለገውን ፡ የካሳ ፡ መጠን ፡ (፮) ፡ (ሐ) ፡ ተከሳሹ ፡ ወይም ፡ በአቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ከተጠሩት ፡ ሌላዎች ፡ ስለ ፡ ካሳው ፡ መጠንና ፡ ተገቢ ፡ መሆን ፡ የሚመሰክሩ ፡ ከሳሹ ፡ ለመጥራት ፡ የሚችል ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ያዝል ። (፯) ፡

እነኚህ ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ አስፈላጊዎቹ ፡ በሙሉ ፡ ስለማይሆኑ ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ድርብ ፡ ክስ ፡ ነገሩ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሰጡት ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ መጨመር ፡ አለባቸው ። በአንቀጽ ፡ ፩፻፶፭ ፡ (ሠ) ፡ ና ፡ (ፀ) ፡ መሠረት ፡ ስለሚጠየቀው ፡ ካሳና ፡ ስለ ፡ ምስክሮቹ ፡ መግለጫ ፡ ነገሮች ፡ ያስፈልጋሉ ። በተጨማሪም ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፶፭ ፡ (፩) ፡ (ሐ) ፡ (መ) ፡ ና ፡ (ረ) ፡ መሠረት ፡ ተጨማሪ ፡ መግለጫዎች ፡ ያስፈልጋሉ ። እንደነዚህ ፡ ያሉትን ፡ መግለጫዎች ፡ ካላገኘ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻውን ፡ ለመቀበል ፡ ላለመቀበል ፡ ለመወሰን ፡ ያስቸግረዋል ። ስለዚህ ፡ አመልካቹ ፡ ተከሳሹ ፡ መቅረብ ፡ እንዳለበት ፡ (፰) ፡ በየትኛውም ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ ካሳውን ፡ እን

---

፫፤ አይደለም ፡ ተብሎ ፡ ካልተነገረ ፡ ከሕግ ፡ የሚጠቀሱት ፡ ሁሉ ፡ ከወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ነው ።

፬፡ ይህ ፡ ተከሳሹ ፡ ከታወቀ ፡ በኋላ ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፳፰) ፡ ክሱ ፡ ከመነበቡ ፡ (፩፻፳፱) ፡ አንቀጽ ፡ ፱ ፡ በፊት ፡ ማመልከቻው ፡ ይቀርባል ፡ ይል ፡ ይመስላል ።

፭፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ በሕጉ ፡ የተረጋገጠ ፡ ባይሆንም ፡ በአንቀጾች ፡ ፩፻፶፬—፩፻፶፱ ፡ መሠረት ፡ ማመልከቻው ፡ መሰማት ፡ ያለበት ፡ በመጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ነው ። ግን ፡ ይህ ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ ይግባኝ ፡ ለተባለበት ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

፮፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ለንብረትና ፡ ለሞራል ፡ ካሳ ፡ የጠየቀ ፡ እንደሆነ ፡ የሁለቱ ፡ ጥያቄዎች ፡ በተራ ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ።

፯፡ ከሳሹ ፡ እንደ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ከምስክሮቹ ፡ የትኞቹ ፡ ለወንጀሉ ፡ የትኞቹ ፡ ደግሞ ፡ ለካሳው ፡ መሆናቸውን ፡ ገልጾ ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ፡ ይኸም ፡ የሆነው ፡ ምስክሮቹ ፡ በአልተጠሩበት ፡ ጉብተው ፡ እንዳይመሰክሩ ፡ ነው ። የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ተጨማሪ ፡ ምስክሮች ፡ ለመቁጠር ፡ ካልፈለገ ፤ በየትኞቹ ፡ ምስክሮች ፡ ነገሩን ፡ ለማጣራት ፡ እንዳሰበ ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ።

፰፤ በውነቱ ፡ ክሱ ፡ ጉዳት ፡ ባደረሰው ፡ ሳይሆን ፡ በሌላው ፡ መቅረብ ፡ አለበት ። ይኸውም ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ መኪና ፡ ነጅ ፡ የራሱ ፡ ያልሆነውን ፡ መኪና ፡ እየነዳ ፡ በችልተኛነት ፡ ሰው ፡ ቢገድል ፤ ካሳው ፡ ከነጂ ፡ ሳይሆን ፡ ከባለመኪናው ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ። (የመኪናው ፡ ባለቤት ፡ በነጂ ፡ ጥፋት ፡ ከሌለ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪፲፻፳፯ ፡ መሠረት ፡ ለካሳው ፡ ኃላፊ ፡ ነው) ።

ደተጠቀቀና ፡ ማስረጃዎቹን ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ፤ ይኸውም ፡ ክሱ ፡ የተፈቀደ ፡ እንደሆነ ፡ ተከሳሹ ፡ ስለክሣው ፡ መከላከያውን ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ ይረደዋል ።

፬፣ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻውን ፡ ተመልክቶ ፤ በራሱ ፡ ሥልጣንም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በአቃቤ ፡ ሕጉ ፡ አሳሳቢነት ፡ ወይም ፡ በተከሳሹ ፤ በአንቀጽ ፡ ፩፻፶፭ ፡ (፩) ፡ ወይም ፡ (፪) ፡ መሠረት ፡ ለመቀበል ፡ የማይቻልበት ፡ ምክንያት ፡ ከተገኘ ፡ ማመልከቻ ውን ፡ አይቀበለውም ። በዚህም ፡ መሠረት ፡ የሚከተሉት ፡ አስተያየቶች ፡ ይሰጡ ፡ ይሆ ናል ።

፭፣ በአንቀጽ ፡ ፩፻፶፭ ፡ (ሀ) ፡ ና ፡ (ለ) ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻውን ፡ የማ ይቀበለው ፡ በጣም ፡ ወጣት ፡ ሰው ፡ ማለት ፡ (አንቀጽ ፡ ፫) ፡ ዕድሜው ፡ በ፲፱ ፡ ና ፡ ፲፭ ፡ ዓመታት ፡ በሆነ ፡ ሰው ፡ ክስ ፡ ሲቀርብ ። የዚህ ፡ መከልከል ፡ ዓላማው ፡ ግልጽ ፡ አይደ ለም ። ወላጆቹ ፡ ወይም ፡ ለወላጆችም ፡ ምትክ ፡ ሁነው ፡ የሚቆጠሩት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔ ር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፹፱ ፡ ና ፡ ፪ሺ፩፻፹፮/ ከሕፃኑ ፡ ጋር ፡ ለጥፋቱ ፡ ኃላፊ ፡ ከሆኑ ፤ የተበደለው ፡ ወገን ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚከ ለከልበት ፡ ምክንያት ፡ አጥጋቢ ፡ አይደለም ፤ ምክንያቱም ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ለጥፋቱ ፡ ኃላፊ ፡ የሆነው ፡ ከሕፃኑ ፡ ጭምር ፡ ለመከሰስ ፡ ስለሚችል ፡ ነው ። ግን ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻ ፶፭ ፡ (፩) ፡ (ሀ) ፡ መሠረት ፡ ለፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ ለወንጀል ፡ ጣምር ፡ ክስ ፡ የሚያስፈል ጉት ፡ ካልተፈጸሙ ፡ ክስ ፡ ይቆያል ፡ የሚለውን ፡ ለማስወገድ ፡ ከሆነ ፡ ክሱን ፡ ላለመቀ በል ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ለወንጀል ፡ ክስ ፡ ዕድሜው ፡ አልደረሰም ፡ ከማለት ፡ (፲፭ ፡ ዓመት) ፡ ለፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ዕድሜው ፡ አይፈቅድም ፡ (፲፰ ፡ ዓመት ፡ ) ማለ ት ፡ ነበር ።

፮፣ ተከሳሹ ፡ ካልቀረበ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻውን ፡ አይቀበለውም ። የዚ ህ ፡ መከልከል ፡ ከለመለመዱም ፡ በላይ ፡ ምክንያቱ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። ምክንያቱም ፡ ክሱ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ተከሳሹ ፡ ቢቀርብ ፡ ባይ ቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጥ ፡ ስለነበረ ፡ ነው ። (፱)

ስለሁለቱም ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ አይቻልም ፡ ብሎ ፡ መደንገግ ፡ ይሻል ፡ ነበር ፤ ምክንያቱም ፡ የማይቀበሉትን ፡ ነገር ፡ ማመልከቻውን ፡ መቀ በልና ፡ ነገሩን ፡ መመልከት ፡ ስለሚያስፈልግ ፡ ነው ። የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ ስለወንጀል ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ ለመክሰስ ፡ ሲፈልግ ፡ ማመልከቻ ፡ ከማቅረቡና ፡ የምስክሮቹን ፡ ዝርዝር ፡ ከመመልከቱ ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቶሎ ፡ መላክ ፡ አለበት ፡ ምክንያቱም ፡ እነዚህ ፡ ዝርዝሮች ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ ለመስ ጠት ፡ ስለማይችሉ ፡ ነው ።

(ለ) ማመልከቻውንም ፡ ነገሩ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከተጀመረ ፡ ወይ ም ፡ ከሳሹ ፡ የሚገባው ፡ ሁኖ ፡ ካልተገኘ ፡ ለማሰናበት ፡ ይቻላል ። የመጀመሪያው ፡ ደንብ ፡ የተመሠረተው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አንድን ፡ መንገድ ፡ ከመረጡ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ለመ ዛወር ፡ አይቻልም ፡ በሚለው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ነው ። የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ካሳው ን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ወይም ፡ በወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊጠይቅ ፡ ሲችል ፤ ከአንዱ ፡

---

፱፣ ይህ ፡ መከልከል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለትንሽ ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ጥፋት ፡ ማመልከቻ ፡ ከቀረበለት ፡ አይቀበል ም ፡ ማለት ፡ ይሆናል ፤ ምክንያቱም ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ተከሳሹ ፡ ግድ ፡ ማቅረብ ፡ የለበትም ፡ (አን ቀጽ ፡ ፩፻፷፰) ወይም ፡ ባይቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ። (አንቀጽ ፡ ፩፻፷ ፱)

ከጠየቀ ፣ ወደ ፣ ሌላው ፣ ለመዛወር ፣ አይችልም ፣ (፲) ነገር ፣ ግን ፣ አስፈላጊዎቹ ፣ ነገሮች ፣ አልተፈጸሙም ፣ በማለት ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ማመልከቻውን ፣ አልቀበልም ፣ ለማለት ፣ ይችላል ።

ይህ ፣ ሊሆን ፣ የሚችለው ፣ ግን ፣ ጉዳዩ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ሳይሆን ፣ በወንጀል ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ የቀረበ ፣ እንደሆነ ፣ ነው ።

(ሐ) በአንቀጽ ፣ ፩፻፶፫ ፣ (፩) (ሠ) ወይም ፣ (ረ) መሠረት ።

የፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ነገር ፣ ያከብደዋል ፣ ወይም ፣ የወንጀሉን ፣ ነገር ፣ ይጐትተዋል ፣ በማለት ፣ የተሰናበተ ፣ ክስ ፣ በወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ በአንቀጽ ፣ ፩፻ ፣ መሠረት ፣ ለመግለጽ ፣ ወይም ፣ ለማብራራት ፣ ይቻላል ። በዚሁም ፣ አንቀጽ ፣ መሠረት ፣ ነገሩ ፣ አስቸጋሪ ፣ ከሆነና ፣ ጥናትም ፣ የሚደረግበት ፣ ሲሆን ፣ ወይም ፣ ያዋቂች ፣ አስተያየት ፣ የሚሰጥበት ፣ ከሆነ ፣ የወንጀሉ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ነገሩን ፣ ወደ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሊያዛውረው ፣ ይችላል (፲፪) ። የፍትሕን ፣ ነገር ፣ ለማካሄድ ፣ ሲባል ፣ የፍትሐ ፣ ብሔርና ፣ የወንጀል ፣ ጣምራ ፣ ክስ ፣ እንደሚፈቀደው ፣ ሁሉ ፣ አልመች ፣ ካለ ፣ ነገሩን ፣ ለመስማት ፣ ማመልከቻውን ፣ መቀበል ፣ አይፈቀድም ።

(መ) ደግሞም ፣ የተጠየቀው ፣ የካሳ ፣ ገንዘብ ፣ መጠኑ ፣ ነገሩን ፣ ከሚያየው ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ሥልጣን ፣ በላይ ፣ ከሆነ ፣ ነገሩን ፣ መቀበል ፣ አይችልም ። ለምሳሌ ፣ የወንጀለኛ ፣ መቅጫን ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፭፻፴፱ ፣ በመቃወም ፣ ጉዳት ፣ ደርሶበት ፣ የተጐዳው ፣ ሰው ፣ $1000 በወረዳ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ለመጠየቅ ፣ አይችልም ። የወረዳው ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ለፍትሐ ፣ ብሔርና ፣ ለወንጀል ፣ ክስ ፣ ከ100 ብር ፣ በላይ ፣ በሆነ ፣ ገንዘብ ፣ ሥልጣን ፣ የለውም ።

እነኝህን ፣ ነገሮች ፣ ነክ ፣ የሆኑትን ፣ ነገሮች ፣ ሁሉ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ማመልከቻውን ፣ አልቀበልም ፣ ማለት ፣ አለበት ። ነገር ፣ ግን ፣ በሁለት ፣ ነገሮች ፣ ጥያቄ ፣ ብቻ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ምርጫ ፣ ሊኖረው ፣ ይችላል ። እነኝህም ፣ ነገሮች ፣ ጥያቄ ፣ (ሀ) በፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ክስ ፣ ለተጠየቀው ፣ ገንዘብ ፣ የሚመሠክሩት ፣ ምስክሮች ፣ በጣም ፣ ብዙዎች ፣ ናቸውን? (ለ) የፍትሐ ፣ ብሔሩን ፣ ክስ ፣ መስማትስ ፣ ነገሩን ፣ አስቸጋሪ ፣ ያደርገዋል ፣ ወይስ ፣ ይጐትተዋል? የሚሉት ፣ ናቸው ፤ ሁለቱም ፣ ጥያቄዎች ፣ አወን ፣ ተብለው ፣ ከተመለሱ ፣ ማመልከቻም ፣ መገደፍ ፣ አለበት ።

---

፲፤ ነገር ፣ ግን ፣ ምርጫው ፣ የግድ ፣ መጨረሻ ፣ ነው ፣ ማለት ፣ አይደለም ። የተጐዳው ፣ ወገን ፣ በወንጀል ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ በወንጀልና ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ክስ ፣ ቢያቀርብም ፤ ፍርድ ፣ ከመስጠቱ ፣ በፊት ፣ ክሱን ፣ አንስቶ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ሊቀርብ ፣ ይችላል ። (አንቀጽ ፣ ፩፻፶፯) በውጭ ፣ አገር ፣ የሚሠራው ፣ እንደሚያመለክተው ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ የቀረበው ፣ ክስ ፣ ለፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ያለ ፣ ሥልጣኑ ፣ ከሆነ ፣ ወይም ፣ በስሕተት ፣ የወንጀልን ፣ ነገር ፣ ወደ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ከሄደ ፣ ነገሩን ፣ ከዚሁ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ አቁሞ ፣ ወደ ፣ ወንጀል ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ለመውሰድ ፣ ይቻላል ። ነገሩ ፣ የቀረበለት ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ነገሩ ፣ በሌላ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ተጀምሮአል ፣ ብሎ ፣ ባለጉዳዮቹ ፣ ካላመለከቱ ፣ ማመልከቻውን ፣ ማስናበት ፣ እንደሌለበት ፣ ማስታወስ ፣ ይጠቅማል ።

፲፩፤ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ የተጐዱት ፣ ወገኖች ፣ ወይም ፣ ክስ ፣ መብት ፣ ያላቸው ፣ የትኞቹ ፣ እንደሆኑ ፣ ለማወቅ ፣ ትንሽ ፣ ያዳግት ፣ ይሆናል ።

፲፪፤ በወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ሥነ ፣ ሥርዓት ፣ መሠረት ፣ ክሱን ፣ የማስናበቱን ፣ ጉዳይ ፣ በወንጀለኛ ፣ መቅጫው ፣ ሕግ ፣ እንደተደነገገው ፣ ምርጫ ፣ ሳይሆን ፣ ጊዲታ ፣ ነው ።

፫፤ አንዳንድ ፣ ሰዎችም ፣ በአንቀጽ ፣ ፩፻፶፫ ፣ ከተመለከቱት ፣ ነገሮች ፣ ምክንያት ፣ በቀ ር ፣ በሌላስ ፣ ማመልከቻው ፣ ይገደፍ ፣ ይሆን ፣ ብለው ፣ ሣያስቡ ፣ አይቀሩም ። በተለይም፣ ተከሳሹ ፣ ከሳሹ ፣ ጉዳዩ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ መታየት ፣ የለበትም ፣ ብሎ ፣ ለመቃወም ፣ እንዳለው ፣ ያለ ፣ መብት ፣ አለ ፣ ወይ ? ተብሎ ፣ ይጠየቅ ፣ ይሆናል ። ይህ ፣ በሕጉ ፣ በደንብ ፣ ያልተገለጠ ፣ ነገር ፣ እንደሚከተለው ፣ መልስ ፣ ሊሰጠው ፣ ይቻላል ።

ተከሳሽ ፣ ነገሩ ፣ ቀደም ፣ ብሎ ፣ በዕርቅ ፣ ወይም ፣ ፍርድ ፣ ተሰጥቶበት ፣ አልቋል ፣ በማለት ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ እንዳያየው ፣ ሊጠይቅ ፣ ይችላል ። እንዲሁም ፣ ነገሩ ፣ በሌላ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ተጀምሮአል ፣ በማለት ፣ እንዳይታይ ፣ ሊጠይቅ ፣ ይችላል ። ወይም ፣ ከሳ ሹ ፣ መብት ፣ የለውም ፣ ወይም ፣ አልተሰጠውም ፣ በማለትም ፣ ሊቃወም ፣ ይችላል ። እን ዲሁም ፣ ዳግም ፣ ነገሩ ፣ በሽማግሌ ፣ ያልቃል ፣ በማለት ፣ ሊቃወም ፣ ይችላል ። ነገር ፣ ግን ፣ በአንቀጽ ፣ ፩፻፶፫ ፣ (፩) ፣ (ሐ) ፣ ና ፣ (መ) ፣ መሠረት ፣ ነገሩ ፣ በሌላ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ይታያል ፣ በማለት ፣ ወይም ፣ ከሳሹ ፣ መብት ፣ የለውም ፣ ከሚሉት ፣ መቃወሞች ፣ በስ ተቀር ፣ ሌላዎቹ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔርና ፣ በወንጀል ፣ ጣምራ ፣ ለሚቀርበው ፣ ክስ ፣ ምን ፣ መልስ ፣ ይሰጣቸዋል ?

(ሀ) ለፍትሐ ፣ ብሔርና ፣ ለወንጀል ፣ ለሚደረገው ፣ ጣምራ ፣ ክስ ፣ ካሳ ፣ የተጠየቀ በት ፣ ነገር ፣ ከሆነ ፣ ማመልከቻው ፣ ይገደፋል ። ነገር ፣ ግን ፣ የወንጀሉ ፣ ክስ ፣ ከመቅረቡ ፣ በፊት ፣ ከፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ክስ ፣ ካሳ ፣ ፍርድ ፣ ተሰጥቶ ፣ እን ደሆነ ፣ የተጐዳው ፣ ወገን ፣ የወንጀሉን ፣ ነገር ፣ በሚያቀርብበት ፣ ጊዜ ፣ ፍት ሐ ፣ ብሔሩ ፣ ፍርድ ፣ ዳግመኛ ፣ እንዲታይ ፣ ለመጠየቅ ፣ አይችልም ። ይህም ነገሩ ፣ በፍርድ ፣ ቤትም ፣ ሆነ ፣ ወይም ፣ ባለ ፣ ጉዳዮቹ ፣ ተስማምተው ፣ ከተፈ ጸመ ፤ ውጤቱ ፣ አንድ ፣ ነው ፤ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ (አንቀጽ ፣ ፫ሺ፫፻፲፱) (፩) ። ነገር ፣ ግን ፣ የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ሥነ ፣ ሥርዓት ፣ የሚለውን ፣ ዓላማ ፣ ከተከተለ ፣ በነገሩ ፣ በመጀመሪያ ፣ ፍርድ ፣ ለመስጠት ፣ የማይቻል ፣ ይመስላል ። ግን ፣ በወንጀል ፣ ጥፋት ፣ ምክንያት ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ካሳ ፣ ከተጠየቀ ፣ የፍ ትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ነገር ፣ የወንጀሉ ፣ ጉዳይ ፣ እስኪያልቅ ፣ መቆየት ፣ አለበት ።

(ለ) ተከሳሹ ፣ የወንጀሉና ፣ የፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ጉዳይ ፣ የፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ክስ ፣ ስለተሰናከለ ፣ በአንድ ፣ ላይ ፣ መታየት ፣ የለበትም ፣ ብሎ ፣ የተቃወመ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ በአንቀጽ ፣ ፱ሺ፩፻፵፫ ፣ (፱) ፣ መሠረት ፣ መቃወ ሙን ፣ ለመሻር ፣ ይችላል ። በወንጀል ፣ ጥፋት ፣ የሚጠየቅ ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ካሳ ፣ የወንጀሉ ፣ ጉዳይ ፣ ካልቆመ ፣ ቆመ ፣ ለማለት ፣ አይቻልምና ፣ ነው ።

(ሐ) ተከሳሹ ፣ ነገሩ ፣ የቀረበበት ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ በቦታ ፣ ምክንያት ፣ ነገሩን ፣ ማየ ት ፣ ሥልጣን ፣ የለውም ፣ ብሎ ፣ የተቃወመ ፣ እንደሆንም ፤ ይህ ፣ መቃወም ፣ ሊሠረዝ ፣ ይቻላል ፤ ምክንያቱም ፣ የተጐዳው ፣ ወገን ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ወ ይም ፣ በወንጀል ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ነገሩን ፣ ለማቅረብ ፣ መብት ፣ ስለአለው ፣ ነው ። የተጐጂ ፣ ምርጫ ፣ ነገሩ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ቀርቦ ፣ ቢ ሆን ፣ ኖሮ ፣ ሥልጣኑ ፣ ለሌላ ፣ ይሆን ፣ ነበር ፣ በሚል ፣ መሠናክል ፣ የለበትም (፲፫) ።

---

፲፫፤ ተከሳሹ ፣ እንደነዚህ ፣ ያሉ ፣ መቃወሞች ፣ ሊያነሳ ፣ የሚችልባቸው ፣ ጉዳዮች ፣ ጥቂቶች ፣ ናቸው ። ምክንያቱም ፣ የሁለቱ ም ፣ ሥልጣን ፣ ስለሚገናኝ ፣ ነው ። የወንጀል ፣ ጥፋት ፣ አብዛኛውን ፣ በተሠራበት ፣ ቦታ ፣ ይታያል ። እንደዚሁ ም ፣ በአልሆነ ፣ ነገር ፣ ለተደረገ ፣ ጥፋት ፣ ካሳ ፣ የሚጠየቀው ፣ በዚሁ ፣ ቦታ ፣ ነው ። ግን ፣ ስለዚህ ፣ ጉዳይ ፣ ግል ጽ ፣ የሆነ ፣ ሕግ ፣ አልወጣም ።

ነገር ፣ ግን ፣ ተከሳሹ ፣ ስለክሱ ፣ ሥረ ፣ ነገር ፣ ስለአለው ፣ ሥልጣን ፣ የተቃወመ ፣ እንደሆነ ፣ ሁለት ፣ ጉዳዮችን ፣ ያስከትላል ። ተከሳሹ ፣ በገንዘቡ ፣ መጠን ፣ በሌላ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ መታየት ፣ አለበት ፣ ብሎ ፣ የታቃወመ ፣ እንደሆነ ፣ በአንቀጽ ፣ ፩፻፵፫ (፱) መሠረት ፣ ይሠራል ። ዳግምም ፣ በክሱ ፣ ሥረ ፣ ነገር ፣ ምክንያት ፣ ሥልጣኑ ፣ የሌላ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ነው ፣ በማለት ፣ የተቃወመ ፣ እንደሆነ ፤ መቃወሙ ፣ አጥጋቢ ፣ ከሆነ ፣ የፍትሐ ፣ ብሔርና ፣ የወንጀል ፣ ጣምራ ፣ ክስ ፣ አይታይም[፲፱] ። እንደሚታወሰው ፣ ሁሉ ፣ አንድ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ነገሩ ፣ የሚያገባው ፣ ከሆነ ፣ መቃወሙ ፣ ከመደረጉ ፣ በፊት ፣ ነገሩን ፣ አልቀበልም ፣ ማለት ፣ አለበት ።

(መ) ክስ ፣ ስለማቅረብ ፣ መጀመሪያ ፣ ስለሚጠየቀው ፣ ፈቃድ ፣ እንደሚታወስው ፣ ሁሉ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ፈቃድ ፣ መጠየቅ ፣ አለበት ፤ በተለይም ፣ በዘመዳሞች ፣ መከከል ፣ ክስ ፣ የተነሣ ፣ እንደሆነ ፣ ነው ። ነገር ፣ ግን ፣ እነዚህ ፣ ነገሮች ፣ ለፍትሐ ፣ ብሔርና ፣ ለወንጀል ፣ የጣምራ ፣ ክስ ፣ ከሚቀርበው ፣ ጉዳይ ፣ የተለዩ ፣ ናቸው ፣ ምክንያቱም ፣ የሚጠየቀው ፣ ፈቃድ ፣ ክሳ ፣ ስለመጠየቅ ፣ ስለአልሆነ ነው ።

(ሠ) በመጨረሻም ፣ ተከሳሹ ፣ ነገሩ ፣ በሽማግሌ ፣ ያልቃል ፣ ሲል ፣ ያመለክት ፣ ይሆናል ፤ ይህም ፣ የፍርድ ፣ ቤቱን ፣ መብት ፣ መቃወም ፣ ይሆን ፣ ይሆናል ። ለእንደዚህ ፣ ያለ ፣ ሁኔታ ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግን ፣ አንቀጽ ፣ ፪ሺ፩፻፵፭ ፣ መመልከት ፣ ያስፈልጋል ። ይህም ፣ አንቀጽ ፣ ጉዳቱ ፣ ከደረሰ ፣ በኋላ ፣ ስለ ፣ ካሣው ፣ ሁለቱም ፣ ወገኖች ፣ ይስማሙ ፣ ይሆናል ፣ የሚል ፣ ነው ። ስምምነቱ ፣ የካሣው ፣ ነገር ፣ በሽማግሌ ፣ ያልቃል ፣ የሚል ፣ ሆኖ ፤ የተጐዳው ፣ ወገን ፣ ያልተስማማ ፣ እንደሆነ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፫ሺ፫፻፵፩ ፣ መሠረት ፣ ለፍትሐ ፣ ብሔርና ፣ ለወንጀል ፣ የጣምራ ፣ ክስ ፣ አይፈቀድም ፣ ይሆን ፣ ይሆናል ።

፱፡ አንድ ፣ የወንጀል ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ በአንድ ፣ ጉዳይ ፣ ላይ ፣ የጣምራ ፣ ክስ ፣ አይደረግበትም ፣ ብሎ ፣ ከወሰነ ፣ ይግባኝ ፣ አይባልበትም ። አንቀጽ ፣ ፩፻፵፫ ፣ (፫) ፣ ይህ ፣ ይግባኝ ፣ እንዳይባል ፣ ብሎ ፣ መወሰን ፣ ተገቢ ፣ ነው ። ተገቢነቱም ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ የሰጠውን ፣ ፍርድ ፣ መቃወም ፣ ጠቃሚ ፣ አይደለም ፣ በማለት ፣ አይደለም ። እንደዚህ ፣ ያለው ፣ ፍርድ ፣ ክስ ፣ ማቅረብን ፣ ጨርሶ ፣ ስለማይከለክልና ፣ ስለካሳው ፣ ስለሚሰጠው ፣ ፍርድ ፣ ለመቃወም ፣ ስለማይችል ፣ ነው ። ይግባኝ ፣ እንዳይባል ፣ ሲባል ፣ የተጐዳውን ፣ ሰው ፣ ካሣ የሚጠይቅበትን ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ የመምረጥ ፣ መብቱን ፣ ብቻ ፣ ይቃወምበታል ፣ እንጂ ፤ ሌላ ፣ ውጤት ፣ የለውም ። የተጐዳው ፣ ሰው ፣ የፍትሐ ፣ ብሔርንና ፣ የወንጀልን ፣ ነገር ፣ ወደ ፣ ወንጀል ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ የመውሰዱ ፣ መንገድ ፣ ቢዘጋበትም ፤ ወደ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ለመውሰድ ፣ ያለው ፣ መብት ፣ ስለአልተነካበት ፣ ነገሩን ፣ ወደ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ሊወስድ ፣ ይችላል ። ከዚህ ፣ ከፍ ፣ ብሎ ፣ እንደተመለከተው ፣ የፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ሕግ ፣ ሥነ ፣ ሥርዓት ፣ ነገሩን ፣ በከለከለው ፣ የወንጀል ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ የወን

---

[፲፱]፡ ይህ ፣ የሚሆነው ፣ በሕጉ ፣ መሠረት ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ክስ ፣ የተጠየቀው ፣ የካሳ ፣ የገንዘብ ፣ መጠን ፣ ነገሩ ፣ ለቀረበለት ፣ ሳይሆን ፣ የሌላው ፣ ሥልጣን ፣ ሲሆን ፣ ነው ። ለምሳሌ ፣ የመንግሥት ፣ ሠራተኞች ፣ በሥራቸው ፣ ላይ ፣ አጥፍተው ፣ ለሚጠየቁበት ፣ ነገር ፣ ሁሉ ፣ በከፍተኛ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ መታየት ፣ አለበት ፣ ይባል ፣ ይሆናል ። እንደዚህ ፣ ያለው ፣ ሕግ ፣ የወንጀሉም ፣ ጥፋት ፣ በከፍተኛ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ መታየት ፣ አለበት ፣ ካላለ ፤ የወንጀልና ፣ የፍትሐ ፣ ብሔርን ፣ ክስ ፣ አጣምሮ ፣ ለማቅረብ ፣ አያስችልም ። በውነቱም ፣ በመጀመሪያው ፣ የወንጀል ፣ ሥነ ፣ ሥርዓት ፣ መሠረት ፣ ጥቂቶቹ ፣ ብቻ ፣ በዚሁ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ይታያሉ ።

ጀሉ ፣ ጉዳይ ፣ ከላለቀ ፣ የፍትሐ ፣ ብሔሩን ፣ መመልከት ፣ አይቻልም ፣ ይል ፣ ይሆናል ።
ስለዚህም ፣ ነገር ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፪ሺ፩፻፺፱ ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ የጥፋት ፣ ሐላፊነትን ፣ በሚወሰንበት ፣ ጊዜ ፣ የወንጀል ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ነገሩን ፣ ያሰናብተው ፣ አያሰናብተው ፣ ነገሩን ፣ ከማየት ፣ አያቆመውም ፣ ይላል ።

## ፪፤ ውጤቶች ።

ለወንጀልና ፣ ለፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ክስ ፣ ጣምራ ፣ ማመልከቻው ፣ ከተፈቀደ ፤ የተጐዳው ፣ ወገን ፣ ከሳሽ ፣ ሆኖ ፣ ይከራከራል ። እርሱም ፣ እንደሌላው ፣ ተከራካሪዎች ፣ ማለት ፣ እንደከሳሽና ፣ እንደተከሳሽ ፣ መብትና ፣ ግዴታዎች ፣ ይኖሩታል ፤ (አንቀጽ ፣ ፩፻፶፮ ፣ (፩) ። ይህም ፣ ማለት ፣ የተጐዳው ፣ ወገን ፣ የክሱን ፣ ቅጅ ፣ በአንቀጽ ፣ ፩፻፱ ፣ (፬) ፣ መሠረት ፣ ያገኛል ፣ ማለት ፣ ነው ። የተጐዳውም ፣ ወገን ፣ በአቃቤ ፣ ሕጉና ፣ በተከላካዩ ፣ ከተጠሩት ፣ ምስክሮች ፣ ስለሚጠይቀው ፣ ካሣ ፣ ለማስመስከር ፣ ምስክሮች ፣ በአንቀጽ ፣ ፩፻፳፬ ፣ መሠረት ፣ ሊቆጠር ፣ ይችላል ። በእንደዚህም ፣ ያለ ፣ ሁኔታ ፣ የተጠሩት ፣ ምስክሮች ፣ በይቀርቡ ፣ በአንቀጽ ፣ ፺፬ ፣ (፪) (ለ) መሠረት ፣ ቀጠሮ ፣ ይቀበላል ። በአንቀጽ ፣ ፩፻፴፯ ፣ መሠረትም ፣ ካልሆነ ፣ መሪ ፣ መሪ ፣ ጥያቄዎችን ፣ የተጐዳው ፣ ወገን ፣ ምስክሩን ፣ ሊጠይቀው ፣ አይችልም ። ከመረታቱ ፣ በፊትም ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ እንዲያውቀው ፣ የተከሳሹን ፣ ያለፈ ፣ ታሪክ ፣ ማውራት ፣ የለበትም ፣ (አንቀጽ ፣ ፩፻፴፰) ። ነገር ፣ ግን ፣ ተከሳሹ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ክስ ፣ ጉዳይ ፣ እንደከሳሹ ፣ ያለ ፣ መብት ፣ አለው ። ለምሳሌ ፣ ስለካሣው ፣ ጉዳይ ፣ መከላከያውን ፣ ለማዘጋጀት ፣ ቀጠሮ ፣ ሊጠይቅ ፣ ይችላል ፤ ወይም ፣ የመከላከያ ፣ ምስክሮችን ፣ ለማቅረብ ፣ ቀጠሮ ፣ ሊጠይቅ ፣ ይችላል ።

ነገር ፣ ግን ፣ በፍትሐ ፣ ብሔርና ፣ በወንጀል ፣ ጣምራ ፣ ክስ ፣ ያለው ፣ ሁኔታ ፣ ረዘምና ፣ ጠለቅ ፣ ያለ ፣ ነው ። በተጠቀሰው ፣ መሠረታዊ ፣ ሕግ ፣ የተጐዳው ፣ ወገን ፣ እንደ ሌሎቹ ፣ ተከራካሪዎች ፣ ሁሉ ፣ ያለ ፣ መብት ፣ ሲኖረው ፤ ስለማስረጃም ፣ እንደዚሁ ፣ ያለ ፣ ያልተለየ ፣ መብት ፣ አለው ። ነገር ፣ ግን ፣ ይህ ፣ መሠረታዊ ፣ ሕግ ፣ በደንብ ፣ ባለመገለጡ ፣ ከሳሹ ፣ መብት ፣ አለው ፣ እንጂ ፣ እንዴት ፣ አድርጎ ፣ እንደሚጠቀምበት ፣ አልተገለጸም ። ይህም ፣ በብዙ ፣ መንገድ ፣ የወንጀለኛ ፣ መቅጫን ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፩፻ ፣ ዓላማ ፣ ዋጋቢስ ፣ ያደርገዋል ። የፍትሐ ፣ ብሔርና ፣ የወንጀል ፣ ጣምራ ፣ ክስ ፣ የያዘ ፤ ማመልከቻን ፣ ቢቀበሉ ፣ ምን ፣ እንደሚሆን ፣ ባለማወቅና ፤ ከሳሹስ ፣ ምን ፣ እንደሚሠራ ፣ ባለማወቅ ፣ የወንጀል ፣ ፍርድ ፣ ቤቶች ፣ ማመልከቻውን ፣ አንቀበልም ፣ ማለቱ ፣ ይሠልጣቸው ፣ ይሆናል ።

በውነቱ ፣ የተጐዳው ፣ ወገን ፣ ሁናቴ ፣ በሁለት ፣ አንቀጾች ፣ ብቻ ፣ በግልጽ ፣ ተነግሯል ። በአንቀጽ ፣ ፩፻፺፪(፩) ፣ መሠረት ፣ የተጐዳው ፣ ወገን ፣ ማስረጃውን ፣ የሚያቀርበው ፣ ዐቃቤ ፣ ሕጉ ፣ ሐሳቡን ፣ ካቀረበ ፣ በኋላ ፣ ነው ። በአንቀጽ ፣ ፩፻፶፮(፪) ፣ መሠረት ፣ ከሳሹ ፣ ስለክሳው ፣ ጉዳይ ፣ ለፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ለማመልከት ፣ የሚችለው ፣ የተከላካዩ ፣ መልስ ፣ ከተሰማ ፣ በኋላ ፣ ነው ። ግን ፣ አንዳንድ ፣ ፍርድ ፣ ቤቶች ፣ እነኝህን ፣ የተሰጡ ፣ መግለጫዎች ፣ የከሳሹ ፣ መብቶች ፣ ከሌላዎቹ ፣ ተከራካሪዎች ፣ አንድ ፣ ለመሆኑ ፣ በጣም ፣ አያስረዱም ፣ ይሉ ፣ ይሆናል ። የወንጀለኛ ፣ ሕግ ፣ ሥነ ፣ ሥርዓት ፣ ያልተሟላ ፣ በመሆኑ ፤ ስለወንጀልና ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ጣምራ ፣ ክስ ፣ ከውጭ ፣ አገር ፣ ሕጎች ፣ ማብራሪያ ፣ ይፈልጉ ፣ ይሆናል ። ነገር ፣ ግን ፣ እንደዚህ ፣ ያሉ ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ሕጎች ፣

የሚሰጡት ፡ እርዳታ ፡ ጥቂት ፡ ነው ። በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ በነሱው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ አይታዩም ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተለየ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ለተጐዱት ፡ ወገኖች ፡ ካሳን ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል(፲፭) ። ነገር ፡ ግን ፡ በውነቱ ፡ የጣምራ ፡ ክስ ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ፤ ምክንያቱም ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ካሳ ፡ የሚጠይቀው ፡ በወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ተከሳሹ ፡ አጥፊ ፡ መሆኑ ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ነው ። ይህም ፡ ማለት ፡ የካሳው ፡ ጉዳይ ፡ ከወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ጋር ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ክርክር ፡ አይቀርብበትም ፡ ማለት ፡ ነው(፲፮) ። በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ግን ፡ ከሳሹ ፡ ስለማስረጃ ፡ ስለአለው ፡ መብት ፡ ጥቂት ፡ ችግሮች ፡ ብቻ ፡ ያጋጥማሉ ። ምክንያቱም ፡ ዋና ፡ ምርመራ ፤ መስቀልኛ ፡ ምርመራና ፡ የድጋሚ ፡ ጥያቄ ፡ የሚል ፡ በሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ውስጥ ፡ ስለሌለ ፡ ነው ። በተለይም ፡ ይህ ፡ ችግር ፡ የሌለው ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ በዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ የቀረበውን ፡ ክስ ፡ ደግፎ ፡ ለመናገር ፡ ስለሚችል ፡ ነው (፲፯) ።

ስለዚህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተመለከተው ፡ አሠራር ፡ ተመሳሳይ ፡ የለውም ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ስለዚህ ፡ ይህንን ፡ ሕግ ፡ በመጥቀስ ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ለሚያጋጥሙት ፡ ችግሮች ፤ ይኸው ፡ የሕግ ፡ መጻፍ ፡ በሚሰጠው ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግና ፡ የጣምራው ፡ ክስ ፡ አላማው ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ በመመልከት ፡ ችግሮቹን ፡ ማስወገድ ፡ ይኖራል ። የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ዋና ፡ ዓላማው ፡ በወንጀል ፡ ጥፋት ፡ ለሚነሱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የኃላፊነት ፡ ውሳኔዎችን ፡ ለማፋጠን ፡ ሊሆንና ፤ የተጐዳውም ፡ ወገን ፡ ካሳ ፡ ለማግኘት ፡ በነገሩ ፡ እንዲከራከር ፡ ስለሚፈቀድለት ፤ ማነኛውም ፡ የጣምራ ፡ ክስ ፡ በሚከተለው ፡ መንገድ ፡ መሠራት ፡ አለበት ።

፩ ፡ ክሱ ፡ ከተነበበ ፡ በኋላና ፡ የተከሳሹ ፡ መልስ ፡ ከተመዘገበ ፡ በኋላ ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፴፪) ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ተከሳሹ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ ካለና ፡ ወይም ፡ ጥፋተኛ ፡ ነኝም ፡ ቢል ፡ ጥፋቱ ፡ ወዲያው ፡ ካልታወቀ ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፴፫ ፡ እና ፡ ፩፻፴፬) ክሱን ፡ ይጀምራል ። ዐቃቤ ፡ ሕጉም ፡ ምስክሮቹን ፡ ይመረምራል ፤ ወይም ፡ ይጠይቃል ። እነዚሁም ፡ ምስክሮች ፡ በተከሳሹ ፡ ከተጠየቀ ፡ በኋላ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በጥያቄው ፡ ለተነሱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ ዳግም ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ፡ (አንቀጾች ፡ ፩፻፴፮ ፡ እና ፡ ፩፻፴፯) ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ከቆጠራቸው ፡ ምስክሮች ፡ አንዱን ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ጉዳይ ፡ ይመሰክራል ፡ ብሎ ፡ ካመለከተ ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፵፩/፪) እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ምስክር ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፴፮ ፡ እንደተመለከተው ፡ በወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ከመሠከረ ፡ በኋላ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩም ፡ ሌሎች ፡ ምስክሮች ፡ ከመጠራታቸው ፡ በፊት ፡ ሊመሠክር ፡ ይችላል ። ግን ፡ ሌላ ፡ መንገድም ፡ ለመከተል ፡ ይቻላል ። ከሳሹ ፡ ምስክሩ ፡ በወንጀሉ ፡ ምስክርነቱ ፡ በሰጠው ፡ ቃል ፡ የመስቀልኛ ፡ ጥያቄ ፡ ከመጠየቁ ፡ በፊት ፡ ሊጠይ

፲፭ ፡ እርከች ፡ በርድ ፡ የወንጀል ፡ አቤቱታ ፤ ማስረጃና ፡ የአሠራሩ ፡ ልምድ ፡ የ፴፪ኛው ፡ እትም ፤ ገጽ ፡ ፪፻፺፩ ፡

፲፮ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ የሚሠራበት ፡ መንገድ ፡ (የሕንድን ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፵፭ ፤ የሱዳንን ፡ አንቀጽ ፡ ፪፻፲፩ ፤ ማላየሲያን ፡ አንቀጽ ፡ ፬፻፹፩ ፤ የደቡብ ፡ አፍሪካን ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፳፱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ ተመልከት ፡) በኢትዮጵያም ፡ መሠራት ፡ ነበረበት ፤ ምክንያቱም ፡ በኢትዮጵያም ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀሉን ፡ ካሳ ፡ ካሳጣራ ፡ የካሳውን ፡ ነገር ፡ አይመለከትም ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፶፭) ።

፲፯ ፡ ለምሳሌ ፡ Code d'instruction criminelle, Art. 335: "A la suite des dépositions dés témoins (. . .), la partie civile ou son conseil et le procureur général seront entendus et développeront *les moyens qui appuient l'accusation*". ተመልከት ።

ቀው ፣ ይችላል ። ከዚያ ፣ በኋላ ፣ የመስቀልኛ ፣ ጥያቄው ፣ ስለወንጀሉና ፣ ስለፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ጉዳይ ፣ በአንድ ፣ ላይ ፣ ሊጠየቅ ፣ ይቻላል ።

በሁለቱም ፣ መንገድ ፣ ለመሥራት ፣ ይቻላል ። ፍርድ ፣ ቤቱም ፣ በታና ፣ ጊዜው ፣ በመመልከት ፣ የተሻለውን ፣ ለመከተል ፣ ይችላል ፤ ምክንያቱም ፣ ይህንን ፣ ወይም ፣ ያንን ፣ ተከተል ፣ የሚል ፣ ሕግ ፣ ስለሌለ ፣ ነው ። ምናልባት ፣ ሁለተኛው ፣ መንገድ ፣ ጉዳዩን ፣ ያዘበራርቃል ፣ ለማለት ፣ ይቻል ፣ ይሆናል ። ደግሞም ፣ ሁለተኛው ፣ መንገድ ፣ አንቀጽ ፣ ፩፻፵፪ ፣ በጥንቃቄ ፣ ከተተረጐመ ፣ ከዚህ ፣ አንቀጽ ፣ ጋር ፣ አይስማማም ፣ ለማለት ፣ ይቻላል ። ይህ ፣ አንቀጽ ፣ የዐቃቤ ፣ ሕጉ ፣ ክስ ፣ ከበቃ ፣ የተጐዳው ፣ ወገን ፣ የራሱን ፣ ክስ ፣ ያቀርባል ፣ ይላል ። ነገር ፣ ግን ፣ የዐቃቤ ፣ ሕጉ ፣ ምስክር ፣ አበቃ ፣ ለማለት ፣ የሚቻለው ፤ ምስክሩ ፣ መልሶ ፣ መላልሶ ፣ ስለወንጀሉ ፣ በተናገረው ፣ ሁሉ ፣ ከተጠየቀ ፣ በኋላ ፣ ነው ። የዐቃቤ ፣ ሕጉ ፣ ምስክር ፣ ስለፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ካሳ ፣ ምስክር ፣ ከሰጠ ፣ ያለ ፣ ዐቃቤ ፣ ሕጉ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ጉዳይ ፣ እንደተሰጠ ፣ ይቆጠራል ። ስለዚህ ፣ ምስክሩ ፣ መጀመሪያ ፣ በከሳሹ ፣ ይጠየቃል ፤ ከዚያም ፣ በኋላ ፣ በተከሳሹ ፣ ተጠይቆ ፣ በከሳሹ ፣ እንደገና ፣ ይጠየቃል ፣ ማለት ፣ ነው ። ስለ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ነገር ፣ ለካሳ ፣ የሚጠየቀው ፣ ምስክር ፣ ከሳሹ ፣ የሚጠይቀው ፣ ጥያቄ ፣ አስፈላጊ ፣ አይደለም ፣ በማለት ፣ ተከሳሹ ፣ ሊቃወም ፣ ይችላል ። ይህንንም ፣ መቃወም ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ በአንቀጽ ፣ ፩፻፵፮ ፣ መሠረት ፣ አስፈላጊውን ፣ መልስ ፣ ሊሰጥ ፣ ይችላል ። ስለማስረጃ ፣ መመዝገብ ፣ የሚደነግገው ፣ አንቀጽ ፣ ፩፻፵፯ ፣ ስለ ፣ ካሳ ፣ በሚሰጠው ፣ ማስረጃም ፣ ጊዜ ፣ ይሠራበታል ።

፪ የዐቃቤ ፣ ሕጉ ፣ ምስክሮች ፣ ከተሰሙ ፣ በኋላ ፣ ስለካሳው ፣ ነገር ፣ ቢጠየቁ ፣ ባይጠየቁም ፤ የተጐዳው ፣ ወገን ፣ ስለፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ካሳ ፣ መጠየቅ ፣ ያለውን ፣ ማስረጃ ፣ ያቀርባል ። በእሱም ፣ ጠያቂነት ፣ የቀረቡትን ፣ ምስክሮች ፣ ያስመሰክራል ። ነገር ፣ ግን ፣ አንድ ፣ ነገር ፣ መታወስ ፣ አለበት ፤ ይኸውም ፣ በአንቀጽ ፣ ፩፻፵፩ ፣ መሠረት ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ዐቃቤ ፣ ሕጉ ፣ ያቀረበው ፣ ክስ ፣ የለምና ፣ ተከሳሹ ፣ መከላከል ፣ አያስፈልገውም ፣ ያለ ፣ እንደሆነ ፣ ነው ። በእንደዚህ ፣ ያለ ፣ ጊዜ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ተከሳሹን ፣ በነጻ ፣ ማሰናበት ፣ አለበት ። ከፍ ፣ ብሎ ፣ እንደተጠቀሰውም ፣ የተከሰሰው ፣ በወንጀል ፣ ካልተፈረደበት ፣ (አንቀጽ ፣ ፩፻፶፰) የካሳ ፣ ፍርድ ፣ አይሰጥበትም ። ስለዚህ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ተከሳሹ ፣ ለቀረበበት ፣ ክስ ፣ መልስ ፣ መስጠት ፣ አለበት ፣ ብሎ ፣ ሲያሳስብ ፣ ብቻ ፣ የተጐዳው ፣ ወገን ፣ ስለሚጠየቀው ፣ ካሳ ፣ ያለውን ፣ ማስረጃ ፣ እንዲያቀርብ ፣ ይጠየቃል ። ይኸም ፣ ማስረጃ ፣ ከዚህ ፣ ከፍ ፣ ብሎ ፣ በተመለከተው ፣ መንገድ ፣ ይካሄዳል ፤ ማለት ፣ ምስክሮቹ ፣ በከሳሹ ፣ መጀመሪያ ፣ ይጠየቁና ፣ በተከሳሹ ፣ የመስቀልኛ ፣ ጥያቄ ፣ ተጠያቂው ፤ እንደገና ፣ በከሳሹ ፣ ደግመው ፣ ይጠየቃሉ ።

---

፲፰፤ ይህም ፣ ሊሆን ፣ የሚችለው ፣ የተጐዳው ፣ ወገን ፣ ጥያቄዎቹን ፣ ሲጠይቅ ፣ ተከሳሽ ፣ ካሳ ፣ መክፈል ፣ እንደሚገባው ፣ በማመልከቻ ፣ ብቻ ፣ ያልተወሰነ ፣ እንደሆነ ፣ ነው ። በውነቱ ፣ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ የተጐዱት ፣ ወገኖች ፣ የአቃቤ ፣ ሕጉ ፣ እረዳት ፣ በመሆን ፣ ተከሳሹ ፣ ጥፋተኛ ፣ መሆኑን ፣ ለማመልከት ፣ ማስረጃ ፣ ሲያቀርቡ ፣ ይታያሉ ። እንደዚህ ፣ ያሉ ፣ ማስረጃዎች ፣ ከመስመራቸው ፣ ውጭ ፣ ስለ ፣ ሆኑ ፣ ለመቀበል ፣ አይቻልም ። እርግጥ ፣ ነው ፤ የሚገባና ፣ የማይገባ ፣ ማስረጃ ፣ ብሎ ፣ ለመወሰን ፣ ብዙውን ፣ ጊዜ ፣ ያዳግት ፣ ይሆናል ። ለምሳሌ ፣ የተጐዳው ፣ ወገን ፣ ተከሳሽ ፣ በማወቅ ፣ ለመሥራቱ ፣ ለማስረዳት ፣ ይፈልግ ፣ ይሆናል ፤ ይኸም ፣ በሞራል ፣ በኩል ፣ ለደረሰው ፣ ጉዳት ፣ በሚጠይቀው ፣ ካሳ ፣ (የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ አንቀጽ ፣ ፪ሺ፩፻፲፮ ፣) በጣም ፣ ይጠቅም ፣ ይሆናል ። ነገር ፣ ግን ፣ አንድ ፣ መታወስ ፣ የሚገባው ፣ ነገር ፣ አለ ፤ ይኸውም ፣ አቃቤ ፣ ሕጉ ፣ ክሱን ፣ በደንብ ፣ ባያካሂደው ፣ የተጐዳው ፣ ወገን ፣ ሥህተቱን ፣ ለማቃናት ፣ አይችልም ። ለማቃናትም ፣ መብት ፣ የለውም ። ነገር ፣ ግን ፣ ተከሳሹ ፣ በዚሁ ፣ በአቃቤ ፣ ሕጉ ፣ ስህተት ፣ ምክንያት ፣ ቢለቀቅም ፤ ስለ ፣ ካሳው ፣ ጉዳይ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ የሚሰጠውን ፣ ፍርድ ፣ አያግደውም ። (የፍትሐ ፣ ብሔር ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፪ሺ፩፻፵፱)፣

፫፤ በተጐዳው ፡ ሰው ፡ ወገን ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ፤በተከላካዩ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ተጀምሮ ፡ ተከሳሹ ፡ ምስክሮቹን ፡ ይጠራል ። እነዚህም ፡ ምስክሮቹ ፡ በወንጀሉ ፡ ነገር ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፵፪ (፪)ና ፡ (፫) የምስክርነት ፡ ቃላቸውን ፡ ይሰጣሉ ። ስለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ የካሳ ፡ ክስ ፡ እንዲመሰክሩ ፡ በተጐዳው ፡ ሰው ፡ የተቆጠሩት ፡ ምስክሮች ፡ በወንጀል ፡ በኩል ፡ ለአለው ፡ ክስ ፡ ምስክርነታቸውን ፡ ከሰጡ ፡ በኋላ ፡ በከሳሹ ፡ ጀማሪነት ፡ ስለካሣው ፡ ይጠየቃሉ ፡ እንዲሁም ፡ ቀጥለው ፡ በተከሳሹ ፡ ከተጠየቁ ፡ በኋላ ፡ መልሰው ፡ ቢያስፈልግ ፡ በከሳሹ ፡ ይጠየቃሉ ።ነገር ፡ ግን ፡ ተከሳሹ ፡ ስለ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ኃላፊነት ፡ ለማስመስከር ፡ ምስክር ፡ የጠራ ፡ እንደሆነ ፡ ይህ ፡ ምስክር ፡ የወንጀሉ ፡ ጉዳይ ፡ ማስረጃው ፡ ከተመዘገበ ፡ በኋላ ፡ ይሰማል ። ይህም ፡ ምስክር ፡ መጀመሪያ ፡ በተከሳሹ ፡ ይጠየቃል ፡ ቀጥሎም ፡ በተጐዳው ፡ ወገን ፡ ይጠየቅና ፡ ቢያስፈልግ ፡ መልሶ ፡ በተከሳሹ ፡ ይጠየቃል ።

፬፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፶፯ (፪) መሠረት ፡ የተጐዳው ፡ ሰው ፡ ስለካሣው ፡ ፍርድ ፡ ያመለክታል ። ቀጥሎም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ የሃላፊነት ፡ ክስ ፡ በአዋፊው ፡ ላይ ፡ እንደተመሰከረበትና ፡ የሚጠይቀውም ፡ ካሣ ፡ የተገባ ፡ መሆኑን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይገልጻል ። በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ይህ ፡ ዓይነት ፡ ማብራሪያ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚቀርበው ፡ ተከላካዩ ፡ የአቤቱታ ፡ ቃሉን ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ነው ። ተከሳሹም ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ መብት ፡ አለው ። ይህ ፡ ሲባል ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚያመለክተው ፡ የመከላከያውን ፡ ማስረጃ ፡ ከወሰደ ፡ በኋላ ፡ ነው? ወይስ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፵፰ (፪) መሠረት ፡ ተከሳሹ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመጨረሻ ፡ ማመልከቻውን ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ነው? ሁለተኛው ፡ መንገድ ፡ ትክክል ፡ ነው ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፵፱ (፩) ተመልከት) ። ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ የማመልከት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ሆኖ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ተከሳሹ ፡ ስለ ፡ ካሣው ፡ ጉዳይ ፡ መልስ ፡ ይሰጣል ፡ ብሎ ፡ መደንገግ ፡ ባላስፈለገም ፡ ነበር ፡ ምክንያቱም ፡ ይህንን ፡ የመጨረሻ ፡ አቤቱታውን ፡ ሲያቀርብ ፡ ሊያደርገው ፡ ስለሚችል ፡ ነው ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የሚሠራበት ፡ መንገድ ፡ ወይም ፡ ቀደም ፡ ተከተሉ ፡ ስህተትን ፡ ለማስወገድ ፡ ተሰውጧል ፡ ማለት ፡ ነው ።

፭፤ ከዚህ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የተሰጡት ፡ አብዛኛዎቹ ፡ መግለጫዎች ፡ በሕዝብ ላይ ፡ በደረሰ ፡ ጥፋት ፡ ሲሠራባቸው ፤ በግልም ፡ ጉዳት ፡ ይሠራባቸዋል ። እነኚህም ፡ መግለጫዎች ፡ ማስረጃ ፡ ላልተገኘለት ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ በተሠራ ፡ ጥፋትም ፡ ይሠራባቸዋል ።

(ሀ) የተጐዳው ፡ ሰው ፡ እንደግል ፡ ክስ ፡ አድርጐ ፡ በሚያቀርበው ፡ በግል ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ነገር ፡ መንግሥት ፡ እንደተደረገው ፡ ክስ ፡ እንደሚታየው ፡ ይታያል ።ነገር ፡ ግን ፡ ከሳሹ ፡ በግሉ ፡ በመንግሥቱም ፡ ነገር ፡ የቆመ ፡ እንደሆነ ፡ በመጀመሪያ ፡ ስለወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ምስክሮች ፡ ቆጥሮ ፡ ከዚያ በኋላ ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ጉዳይ ፡ ምስክሮች ፡ ይቆጥራል ።ነገር ፡ ግን ፡ ለወንጀሉ ፡ የተቀጠሩት ፡ ምስክሮች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩም ፡ ካሣ ፡ የሚመሠክሩ ፡ ከሆነ ፡ ስለወንጀሉ ፡ በሰጡት ፡ ቃላቸው ፡ ደጋግመው ፡ ተጠይቀው ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ስለካሣው ፡ ሊመሠክሩ ፡ ይችላሉ (፲፱፤) ።

(ለ) ከፍ ፡ ብሎ ፡ እንደተመለከተው ፡ ተከሳሹ ፡ አጥፍቻለሁ ፡ ብሎ ፡ ካመነ ፤ በአቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ሆነ ፡ በተከላካይ ፡ ማስረጃ ፡ ሳይቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካልተቃወመ ፡

---

፲፱፤ እንደሚታወሰው ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ማስረጃ ፡ አቀራረብ ፡ የተሰጡት ፡ መግለጫዎች ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተሻለ ፡ መንገድ ፡ ካገኘ ፡ እንደምርጫው ፡ እንዳይሠራ ፡ አይከለክለውም ።

በቀር ፡ በራሱ ፡ እምነት ፡ ሊፈረድበት ፡ ይችላል (፳፩) ። ይህም ፡ ሲባል ፡ የተጐዳውን ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ለማሰናከልና ፡ ለመጉዳት ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፵፱ ፡ (፫) መሠረት ፡ ስለቅጣቱ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከማመልከቱ ፡ በፊት ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ክሱን ፡ ይጀምራል ፡ ማለት ፡ ነው ። ከሳሹ ፡ በአቃቤ ፡ ሕጉና ፡ በተከላካዩ ፡ ከቀረቡት ፡ ምስክሮች ፡ መካከል ፡ አንዳንዶቹ ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ባይሰጥ ፡ ኑሮ ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ክሣ ፡ ይመሠክሩ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ከሠበ ፤ እነኝህ ፡ ምስክሮች ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ በሚሠራበት ፡ መንገድ ፡ ቃላቸውን ፡ ይሠጣሉ ። ልዩነቱ ፡ ስለከሣው ፡ የሚሰጠው ፡ የሚቀርበው ፡ ማስረጃ ፡ ከፍርዱ ፡ በኋላ ፡ እንጂ ፡ በፊት ፡ አይሰማም ። የተጐዳውም ፡ ወገን ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሐላፊነት ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማመልከት ፡ መብት ፡ አለው ። ተከሳሹም ፡ እንደዚሁ ፡ ለመመለስ ፡ መብት ፡ አለው ። ይህም ፡ መብት ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉና ፡ ተከሳሹ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፵፰ የመጨረሻ ፡ ሃሣባቸውን ፡ ከመስጠታቸው ፡ በፊት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

## ፫ ፡ ፍ ር ድ ።

ዐቃቤ ፡ ሕጉና ፡ ተከሳሹ ፡ ያላቸውን ፡ የመጨረሻ ፡ ጉዳይ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከመለከቱና ፡ ከሳሹም ፡ ስለሚጠይቀው ፡ ካሳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ከጠየቀ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ፤ (አንቀጽ ፡ ፩፻፵፱/፩) ። ቅጣቱም ፡ በቀረቡት ፡ ማስረጃዎች ፡ መሠረት ፡ ይሠጣል ፤ (አንቀጽ ፡ ፩፻፵፱/፫) (፳፪) ። ከፍ ፡ ብሎ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተከሳሹ ፡ በወንጀል ፡ አጥፍቶ ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ካሳ ፡ ፍርድ ፡ አይሰጥም ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፶፰) ። ተከሳሹ ፡ በወንጀሉ ፡ ክስ ፡ አጥፍቶ ፡ ካልተገኘ ፡ ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ ነገሩን ፡ ማቅረብ ፡ አለበት (፳፫) ። የተጐዳው ፡ ወገን ፡ በክሱ ፡ ከረታ ፡ ፍርዱ ፡ የሚከተሉትን ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ። (ሀ) ስለ ፡ ወንጀሉ ፡ ነገር ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፵፱ ፡ መሠረት ፡ የተፈለጉትን ፡ ጉዳዮችና ፡ (ለ) ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ነገር ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፶፱ ፡ የተፈለጉትን (፳፬) ።

(ሀ) የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ካሳ ፡ ለመስጠት ፡ ብቻ ፡ ተወስኗል ። ስለዚህም ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሌላ ፡ ከወንጀል ፡ ሥራ ፡ ከሚመነጭ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡

---

፳፩ ነገር፡ግን ፡ ስለ ፡ ተከሳሹ ፡ ጠባይም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የአለፈ ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ማስረጃ ፡ ጥፋቱ ፡ ከተረጋገጠም ፡ በኋላ ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ። (አንቀጽ ፡ ፩፻፵፱) (፫)ና ፡ (፬)

፳፪ ይኸን፡ከፍ ፡ ብሎ ፡ የተመለከተውን ፡ ጉዳይ ፡ አይቃወመውም ። ተከሳሹ ፡ በራሱ ፡ እምነት ፡ ከተፈረደበት ፡ ከሳሹ ፡ በፍርድ ፡ ጥፋቱ ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ እንጂ ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ አያመለክትም ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፵፱ ፡ (፩)።

፳፫ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፵፫ (፪) ከወንጀል ፡ ሥራ ፡ የተነሱ ፡ ለመሥራት ፡ የተወሰኑ ፡ የሚለው ፡ ነገሩ ፡ የተሰናበተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይሠራበት ፡ አይሠራበት ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። ምክንያቱም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ክሣው ፡ ከወንጀሉ ፡ ጥፋት ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ። የፈረንሳይ ፡ ከፍተኛ ፡ የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በኔ ፡ ፯ ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ በአወጣው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ የወንጀሉ ፡ ነገርም ፡ ቢሰናበት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ነገር ፡ እስከ ፡ ተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ሊታይ ፡ ይችላል ፡ ብሏል ።

፳፬ አንቀጽ ፡ ፩፻፶፱ ፡ አልተሟላም ፤ ምክንያቱም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ የካሣ ፡ ጉዳይ ፡ የሚያየው ፡ የወንጀል ፡ ፍ/ቤት ፡ ጉዳዩ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍ/ቤት ፡ ሊታይ ፡ እንደሚገኘው ፡ ያለ ፡ ማብራሪያ ፡ ስለማይገኝ ፡ ነው ፤ (ለምሳሌ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ የሰጠበት ፡ ምክንያቶች ፤ በየትኛው ፡ አንቀጽ ፡ እንደፈረደና ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ መግለጫዎች ፡ መስጠት ፡ ነበረባቸው)

ነገር ፡ መግባት ፡ የለበትም ፡ (፳፱) ። ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በመጥለፍ ፡ ምክንያት ፡ ጥፋ ት ፡ አጥፍቶ ፡ ቢገኝና ፤ የተጠለፈችውም ፡ ከዚሁ ፡ ሰው ፡ አርግዛ ፡ ብትገኝ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፯፻፶፰ ፡ መሠረት ፡ የወንጀሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ልጁ ፡ የዚህ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለመፍረድ ፡ አይችልም ። እንደዚሁም ፡ በዝሙትነት ፡ ምክንያት ፡ ተከሳሹ ፡ አባት ፡ ላለመሆኑ ፡ የሚያሳዩ ፡ ማስረጃዎች ፡ ቢቀርቡም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በፍ ትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፯፻፹፱ ፡ መሠረት ፡ ተካሹ ፡ ልጇ ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ ማመልከቻ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ፈቃድ ፡ አይሰጥም ።

(ለ) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከጥፋት ፡ ለደረሰ ፡ ጉዳት ፡ ካሳ ፡ ሊያሰጥ ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፡ በቸልተኛነት ፡ ሰው ፡ በመግደል ፡ በተደረገ ፡ ጥፋት ፡ ላይም ፡ የንብረት ፡ ጉዳት ፡ ቢደ ርስ ፡ የነፍስ ፡ ካሳ ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ንብረቱ ፡ ካሳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊያሰጥ ፡ አይችልም ። እንዲያውም ፡ በቸልተኝነት ፡ ምክንያት ፡ የደረሰ ፡ ጉዳት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በአናቀጽ ፡ ፳፻፵፫ ፡ እንደተመለከተው ፤ የወንጀል ፡ ጥፋትን ፡ ኃላፊነት ፡ አያስከትልም ። ይህ ፡ አንቀጽ ፡ የወንጀል ፡ ጥፋት ፡ የሚያደርገው ፡ በማወቅ ፡ የተሠራን ፡ ጥፋት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በወንጀል ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ኃላፊነት ፡ ካልተነ ሳ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻ ፡ መሠረት ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ካሳ ፡ ሊያሰጥ ፡ የሚለው ፡ ሕግ ፡ አልተሠራበትም ፡ ማለት ፡ ነው (፴) ።

(ሐ) ካሣም ፡ በሚያሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለግምቱና ፡ ስለ ፡ ካሣው ፡ አከ ፋፈል ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የሚገኘውን ፡ ሕግ ፡ ይከተላል ። ለምሳሌ ፡ የሚቄ ፡ ወገ ኖች ፡ ካሣ ፡ የጠየቁ ፡ እንደሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ ለካሣ ፡ ይከ ፈል ፡ ብሎ ፡ አያዝም ፡ እንጂ ፡ ለመተዳደሪያ ፡ የሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ ይከፈል ፡ ብሎ ፡ ለማ ዘዝ ፡ ይችላል ፡ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፺፭) ፡ ለሞራል ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ የተጠየቀ ፡ እንደሆነ ፡ ለካሣ ፡ የሚሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ከ$ 1000 አይበልጥም ፤ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፲፮ ፡ (፫) ።

(መ) ከሳሽ ፡ በነገሩ ፡ የረታ ፡ እንደሆነ ፤ ተከሳሹ ፡ ነገሩ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ቢሆን ፡ ኑሮ ፡ የሚከፍለውን ፡ የፍርድ ፡ ቤትና ፡ የሌላውንም ፡ ወጭ ፡ መክ ፈል ፡ አለበት ፤ (አንቀጾች ፡ ፩፻፶፱ና ፡ ፪፻፺፱) ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሳሹ ፡ ሣይረታ ፡ የቀረ ፡ እን ደሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ገንዘብ ፡ ከመክፈሉም ፡ በላይ ፡ ተከሳሹ ፡ ያወጣ ውን ፡ ወጭም ፡ ይከፍላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ለፍርድ ቤት ፡ የሚከፍለው ፡ ገንዘብ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የወንጀል ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ሲቀርብ ፡ የሚከፈለው ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፶፱ ፡ (፩) ግን ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ የሚከፈለው ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፶፱(፩)ለ) እንዲሁም፡ ሌላው ፡ ወጭ ፡ ነገሩ ፡ የተሰናበተ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ የተለቀቀ ፡ እንደሆነ ፡ እንዴት ፡ እንደሚከፈል ፡ አልተነገረም ። ሁኔታው ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ገንዘቡ ፡ በ ሙሉ ፡ በከሳሹ ፡ መጀመሪያ ፡ ተከፍሎ ፡ በጉዳዩ ፡ የረታ ፡ እንደሆነ ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ በተከሳሹ ፡ እንዲከፈል ፡ የሚል ፡ ይመስላል ።

፳፱፤ ይህ ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳይ ፡ በጣምራ ፡ እንዲታይ ፡ ባይፈቀድም ፡ የሚሠራበት ፡ መሠረታዊ፡ ሕግ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ኃላፊ ፡ ሆኖ ፡ ካላገኘው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፶፭፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተከሳሹ ፡ ሊፈርድበት ፡ አይችልም ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ይህንኑ ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግ፡ መዝለል ፡ አለመዝለል ፡ ያስፈልግ ፡ እንደሆነ ፡ በማለት ፡ ክርክር ፡ ይነሣል ።

፴፤ ነገር ፡ ግን፡ በወንጀል ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፹፱ ፡ ትርጕም ፡ መሠረት ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጥፋቶች፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ሲገኙና ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ እንጂ ፡ ነፍስ ፡ በማጥፋቱ ፡ ላይ ፡ የተገኘው ፡ ጥፋት ፡ ያለውቀት ፡ ከሆነ ፡ የነፍስ ፡ ዋጋና ፡ የንብረቱም ፡ ዋጋ ፡ ሊታዘዝ ፡ ይቻላል ።

(ሥ) የተጐዳው ፡ ወገን ፡ በግሉ ፡ እንጂ ፡ በመንግሥት ፡ በሆነው ፡ ነገር ፡ ጨምሮ ፡ ካልተከራከረ ፡ ስለወንጀሉ ፡ ክስና ፡ ስለ ፡ ካሳው ፡ በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ስለወንጀሉ ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ አይቻልም (፳፮) ። ለማድረግ ፡ የሚችለው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካሳ ፡ አላሰጠው ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ ይግባኝ ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፹፮/፩) ። ወይንም ፡ ካሳ ፡ ቢሰጥም ፡ ስለ ፡ ካሳው ፡ መጠን ፡ ይግባኝ ፡ ማለት ፡ ይችላል ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፹፮/፫) ። ነገር ፡ ግን ፡ የሁለተኛው ፡ ዓይነት ፡ ይግባኝ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፹፫ ፡ መሠረት ፡ መሆን ፡ አለበት ። ተከሳሹ ፡ ግን ፡ በወንጀሉ ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ ሳይል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካሳ ፡ በማዘዙ ፡ ወይም ፡ ስለአዘዘው ፡ የካሳ ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ይግባኝ ፡ ሊል ፡ ይችላል ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፹፮/፬) ። ስለካሳው ፡ የሚደረገው ፡ ይግባኝ ፡ ለወንጀሉ ፡ ጉዳይ ፡ ይግባኝ ፡ ሲባል ፡ አብሮ ፡ ይሄዳል ፡ (፳፯) በወንጀሉ ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ ባይባልም ፤ ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ጉዳይ ፡ ሥልጣኑ ፡ ወደሆነው ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፹፮/፩ ። ስለካሳ ፡ ጉዳይ ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ በሚሰማበት ፡ ጊዜ ፡ በወንጀሉ ፡ ተከሳሹ ፡ ካልተረታ ፡ ካሳ ፡ ሊሰጥ ፡ አይችልም ። ይህም ፡ ማለት ፡ ተከሳሹ ፡ ስለወንጀሉ ፡ ክስና ፡ ስለካሳው ፡ ጉዳይ ፡ ይግባኝ ፡ ብሎ ፡ ሳለ ፡ የወንጀሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀሉን ፡ ካሳ ፡ ካሰናበተው ፤ ስለካሳውም ፡ ያለውን ፡ ይግባኝ ፡ ማሰናበት ፡ አለበት ። ግን ፡ ስለካሳው ፡ ጉዳይ ፡ በወንጀሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ቢሰናበት ፡ ሥልጣን ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ሊባል ፡ ይቻላል (፳፰) ።

(ረ) ግን ፡ ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ካሳና ፡ ስለሌላዎችም ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደተሰጠ ፡ መቆጠርና ፡ መፈጸም ፡ አለበት ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፲) ። ይኸም ፡ ይደረጋል ፡ ሲባል ፡ እንዲከፍል ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ገንዘቡን ፡ ለመክፈል ፡ ችሎታ ፡ ሲኖረው ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በወንጀል ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፩ ፡ መሠረት ፡ ለፍርድ ፡ ቤትና ፡ ለሌላ ፡ ወጭ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ሳይሆን ፡ ለካሳ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ከጠየቀ ፡ ከተፈረደበት ፡ ሰው ፡ የተወረሱት ፡ ዕቃዎች ፡ ተሸጠው ፡ ያስያዘውና ፡ በመቀጫ ፡ የከፈለው ፡ ገንዘብም ፡ ተጨምሮ ፡ ይከፈላል (፳፱) ። ነገር ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ማመልከቻ ፡ ሲቀርብለት ፡ የሕግ ፡ ርዳታ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ እንደሚመረምረው ፡ ሁሉ ፡ ስለተፈረደበት ፡ ሰው ፡ የሀብት ፡ ሁኔታ ፡ ማጥናት ፡ አለበት ። ስለዚህም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በአዘዘው ፡ መሠረት ፡ ስለተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ድሀ ፡ መሆን ፡ የቀረበው ፡ ራፖር ፡ አጥጋቢ ፡ ሆኖ ፡ ካላገኘው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወንጀል ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፩ ፡ መሠረት ፡ ካሳ ፡ እንዲከፍል ፡ ማዘዝ ፡ የለበትም ። ስለድህነት ፡

---

፳፮፤ በመንግሥት ( በኩል ) በተደረገው ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ አቃቤ ( ሕጉ ፡ ክስ ) ካላቀረበ ( የተጐዳውን ) ወገን ፡ ክስ ፡ አቅርብ ፡ ብሎ ፡ መብት ፡ ሊሰጠው ፡ አይችልም ፤ አንቀጽ ፡ ፻፱(፩) ፡ አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወንጀሉን ፡ ቢያቆም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ሳለው ፡ ሥራ ፡ አይደለም ። በመንግሥት ፡ በኩል ፡ ስለአለው ፡ ካሣ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ ነገሩን ፡ ለመከታተል ፡ ወይም ፡ ለመተው ፡ የአቃቤ ፡ ሕጉ ፡ መብት ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ …ቀጽ ፡ ፩፻፹፮ ፡ እንደሚለው ፡ ስለ ፡ ወንጀሉ ፡ ጉዳይ ፡ ለማመልከት ፡ ወይም ፡ ለመከራከር ፡ የሚችሉት ፡ የሚገባቸው ፡ ወይም ፡ የተጐዱት ፡ ወገኖች ፡ ማለት ፡ አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ ናቸው ፤ እንደ ፡ አቃቤ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ የማይከራከረው ፡ የይግባኝ ፡ ሥልጣኑም ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ካሣ ፡ ብቻ ፡ ይነጋገራል ። የይግባኝ ፡ ሥልጣኑም ፡ በተለየ ፡ አንቀጽ ፤ ማለት ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፹፮ ፡ ተመልክቷል ።

፳፯፤ መጀመሪያ ፡ ክሱ ፡ የቀረበበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀሉንና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ ከፈቀደ ፡ ይግባኝ ፡ የተባለበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የጣምራውን ፡ ክስ ፡ መቀበል ፡ አለበት ፡ እንጂ ፡ አልቀበልም ፡ ማለት ፡ የለበትም ። ይኸውም ፡ ይግባኝ ፡ የተባለበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የካሳው ፡ ይግባኝ ፡ የወንጀሉን ፡ ክስ ፡ ያቆየዋል ፡ ወይም ፡ ያክብደዋል ፡ ብሎ ፡ አልቀበልም ፡ ማለት ፡ አይችልም ።

የቀረበውን ፡ ማመልከቻ ፡ ወይም ፡ ልመና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከተቀበለው ፡ መንግሥቱ ፡ ስለተፈረደበት ፡ ድሀ ፡ ለከሣሹ ፡ ያልፋል ፤ (የወንጀኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፩(፫)።

፪ በወንጀልና ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ የሚነሱት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ችግሮች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ አስቸጋሪነታቸው ፡ ከዚህ ፡ ያነሰ ፡ ይነሱ ፡ ይሆናል ። በተለይም ፡ እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ችግሮች ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ ተፈቅዶ ፤ የወንጀሉ ፡ ነገር ፡ ሲያቆም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ነገር ፡ የቀጠለ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ችግሮች ፡ የሚገኙት ፡ በተለይም ፡ ተከሳሹ ፡ የሞተ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ምሕረት ፡ የተደረገለት ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህም ፡ ችግሮች ፡ መሠረታዊ ፡ የሆነውን ፡ የጣምራ ፡ ክስ ፡ ደንብ ፡ በመከተል ፡ ሊወገዱ ፡ ይችላሉ ።

(ሀ) ተከሳሹ ፡ ሳይፈረድበት ፡ ወይም ፡ ጥፋተኛ ፡ መሆኑ ፡ ሳይረጋገጥ ፡ የሞተ ፡ እንደሆነ ፡ በመንግሥት ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ክስ ፡ ይቆማል ። በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፪፻፳፫ ፡ መሠረት ፡ ተከሳሹ ፡ ከሞተ ፡ ክሱም ፡ አይቀጥልም ፡ ፍርድም ፡ አይሰጥም(፴)። ነገር ፡ ግን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ክስ ፡ በሟቹ ፡ ወራሾች ፡ ላይ ፡ ሊቀጥል ፡ ይችላል ፡ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፺፬ (፫) ። ነገር ፡ ግን ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩን ፡ በመቀጠል ፡ ያየው ፡ ይሆን ፡ ወይ? ብሎ ፡ መጠየቅን ፡ ያስከትላል ። በፈረንሣይ ፡ አገር ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ከፍተኛ ፡ የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ (የፈረንሣይ) ፡ በየካቲት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፯ ፡ በወሰነው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፤ መልሱ ፡ ለማየት ፡ ወይም ፡ ለመቀጠል ፡ የወንጀሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይችል ፡ ነበር ። በኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ መልሱ ፡ ሊያይ ፡ አይችልም ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የወንጀል ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ የቀረበለት ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀሉ ፡ ጥፋት ፡ መሠራቱ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ካሣ ፡ ሊሰጥ ፡ አይችልም ፡ ስለተባለ ፤ ተከሳሹ ፡ የወንጀል ፡ ሥራው ፡ ከመረጋገጡ ፡ በፊት ፡ ከሞተ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ የማየት ፡ ሥልጣኑ ፡ ወዲያውኑ ፡ ያቆማል ። ነገር ፡ ግን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ክስ ፡ ለወንጀሉ ፡ የተሰጠውን ፡ ያህል ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ይሰጠዋል ። ምክንያቱም ፡ ይህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ የተነሳው ፡ ከወንጀሉ ፡ በደል ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

፳፰ ፡ ግን ፡ ተከሳሹ ፡ በወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ተረትቶ ፡ በወንጀሉ ፡ እንኳ ፡ በካሳው ፡ ይግባኝ ፡ ቢልና ፡ በኋላ ፡ ነፃ ፡ ቢወጣ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ ይነሳል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይግባኝ ፡ ተብሎበት ፡ የወንጀሉን ፡ ጉዳይ ፡ ያሰናበተው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ተስማምተው ፡ የተቀበሉትን ፡ ማለት ፡ ይግባኝ ፡ ያልተባለበትን ፡ የካሣ ፡ ክስ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፶፯ ፡ ወንጀሉን ፤ ያሠናበተ ፡ ካሣውን ፡ ማሰናበት ፡ አለበት ፡ ስለእለ ፡ ማሰናበት ፡ አለበትን ? መልሱ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ፡ የማለት ፡ ይመስላል ። አንደኛ ፡ ያልቀረበለትን ፡ ነገር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማየት ፡ የለበትም ። ሁለተኛም ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፶፰ ፡ የሚከለክለው ፡ የወንጀሉንና ፡ የካሳውን ፡ ነገር ፡ የሚያየው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀሉን ፡ ክስ ፡ ካሰናበተው ፡ ካሳ ፡ መስጠት ፡ የለበትም ፤ ብሎ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀሉን ፡ ክስ ፡ ማሰናበትና ፡ የካሳ ፡ ገንዘብ ፡ ማስከፈል ፡ የለበትም ። ሕጉ ፡ በየትም ፡ ቦታ ፡ ቢሆን ፡ አንድ ፡ ይግባኝ ፡ ያልተባለበት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የካሳ ፡ ፍርድ ፡ ተከሳሹ ፡ ይግባኝ ፡ ብሎ ፡ በወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ቢለቀቅ ፡ የካሳው ፡ ጉዳይም ፡ ይሰናበታል ፡ የሚል ፡ የለም ።

፳፱ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፩ ፡ የተመለከተው ፡ ደንብ ፡ በ፩ሺ፱፻፵ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ፡ኤ፡አ፡ በወጣው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መግቢያ ፡ በአንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ ይገኝ ፡ ነበር ።

፴ ግን ፡ ከሳሹ ፡ ቢሞት ፤ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፵፬(፪) ፡ መሠረት ፡ ከሞተ ፡ የመክሰሱ ፡ መብት ፡ ካልቆመ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፵፬(፭) ፡ መሠረት ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ክስ ፡ ወራሾቹ ፡ ሊነጋገሩ ፡ ይችላሉ ።

(ለ) የይቅርታ ፣ ወይም ፣ የምሕረት ፣ ሕግ ፣ ከወጣበት ፣ ጊዜ ፣ ጀምሮ ፣ ክሱን ፣ ያቆመዋል ፤ (የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፪፻፺፯ (፪) ። በዚህም ፣ ጊዜ ፣ በሞት ፣ ምክንያት ፣ እንደተሠራው ፣ ይሠራል ። ግን ፣ ምሕረት ፣ ክሱን ፣ ስለሚያስቀረውና ፣ (የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፪፻፺፯(፪) ) ክስ ፣ ቀርቦበት ፣ የነበረውንም ፣ የወንጀል ፣ ጥፋት ፣ እንዳልተሠራ ፣ ስለሚያስቆጥረው ፣ ከዚሁ ፣ የወንጀል ፣ ጥፋት ፣ የተነሣው ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ክስ ፣ ከወንጀሉ ፣ ጥፋት ፣ የተነሣ ፣ ነው ፣ ለማለት ፣ አይቻልም ። ስለዚህ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ በአንቀጽ ፣ ፪ሺ፩፻፺፫ (፪) መሠረት ፣ የፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ክስ ፣ በወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ የተወሰነ ፣ የይርጋ ፣ ጊዜ ፣ የለውም ። የፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ የይርጋ ፣ ጊዜ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ በአንቀጽ ፣ ፪ሺ፩፻፺፫ (፩) በተመለከተው ፣ የይርጋ ፣ ጊዜ ፣ ብቻ ፣ ነው ፣ የተወሰነው ። ተከሳሹ ፣ ጥፋተኛ ፣ መሆኑ ፣ ከተረጋገጠ ፣ በኋላ ፤ የተደረገ ፣ ምህረት ፣ የፍትሐ ፣ ብሔሩን ፣ የካሣ ፣ ገንዘብ ፣ ከመክፈል ፣ አያግድም ፣ (የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፪፻፺፩) ።

የፍትሐ ፣ ብሔርና ፣ የወንጀል ፣ ጣምራ ፣ ክስ ፣ የሚካሄድበት ፣ መንገድ ፣ እንደሌሎቹም ፣ አገሮች ፣ በኢትዮጵያም ፣ ታሪካዊ ፣ ምክንያት ፣ አለው ። ይህም ፣ መንገድ ፣ ወይም ፣ አሠራር ፣ ያለ ፣ ጥርጥር ፣ በወንጀል ፣ ሥራ ፣ ለተጐዱት ፣ ወገኖች ፣ ጠቃሚነት ፣ አለው ። ነገር ፣ ግን ፣ የወንጀል ፣ መቅጫን ፣ ሕግ ፣ ሥነ ፣ ሥርዓት ፣ ተገቢ ፣ አንቀጽ ፣ እየተከተሉ ፣ በሚሠራበት ፣ ጊዜ ፣ የፈረንሳይ ፣ የሕግ ፣ ሊቅ ፣ «ከግል ፣ ጥቅም ፣ የጠቅላላ ፣ ጥቅም ፣ መቅደም ፣ አለበት» ያለውን ፣ ማስታወስ ፣ ይገባል ።